# ጥናት አንድ ዮናስ 1፡1-16 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዮናስ የተቀበለው ተልዕኮ ወደ ታላቂቱ ከተማ ወደ ነነዌ እንዲሄድና በእርሷ ላይ እንዲሰብክ ነበረ፡፡ ይህም ተልዕኮ ወደ ነብዩ የመጣበትን መንገድ ክፍሉ ሲነግረን ‹‹የእግዚአብሄር ቃል›› ወደ እርሱ እንደመጣ ነው፤ ማለትም በቃል ነው የመጣለት፡፡
2. ነብዩ ዮናስ ወደ ተርሴስ በመኮብለል እግዚአብሄር ከማይደርስበት ቦታ እድረሳለሁ ብሎ እንዳሰበ አይመስለኝም፤ ነገር ግን ይህንን ዓይነት ተልዕኮ ከመውሰድ ለጊዜው ለመሸሽና ሃላፊነቱ ለሌላ ሰው እንዲተላለፍ ጊዜያዊ መፍትሄን ለራሱ ለመስጠት እንደሚሆን ነው የሚመስለኝ፡፡
3. ለእግዚአብሄር ሲታዘዙ የምናያቸው ነገሮች፡ ባህር፣ ነፋስ፣ ማዕበሉ ሲሆኑ ያልታዘዘ የምናየው ዮናስ ብቻ ነው፡፡ መናወጡን ለማቆም የተወሰዱት እርምጃዎች፣ እያንዳንዱ ወደ አምላኩ መጮሁ፣ በመርከቢቱ ውስጥ የነበረውን ዕቃ ወደ ባህር መጣል፣ ዮናስም አምላኩን እንዲጠራ ማሳሰብ፣ ምክንያቱን ለማወቅ ዕጣ መጣጣል ሁሉ አድርገዋል፡፡
4. ይህ ሁሉ መራወጥ፣ ጸሎትና ንብረትን ወደ ባህር መወርወር በተካሁደበት ወቅት ዮናስ በመርከቢቱ ታችኛ ክፍል በመግባት እንቅልፉን ይለጥጥ ነበረ፡፡ ከዚህ እኔ የምማረው ነገር ቢኖር፤ ከእግዚአብሄር ፈቃድ ውጭ በሆንን ቁጥር እንቅልፍ ወይም ሰላም እናጣለን፣ ወይም ደግሞ ነገሮች ሁሉ አይሳኩልንም ማለት ላይሆን እንደሚችል፤ ወይም ደግሞ የሰላም እንቅልፍ ተኛን ማለት በጌታ ፈቃድ ውስጥ መሆናችንን እንደማያመለክት እማራለሁ፡፡
5. ዮናስ የተጠየቃቸው ጥያቄዎች አምስት የሚሆኑ ሲሆኑ እነዚህም፤ ይህ ሁሉ በማን ምክንያት መጣብን? ሥራህ ምንድነው? ከወዴት ነው የመጣኸው? አገርህ የት ነው? ከየትኛው ሕዝብ ነህ? የሚሉ ናቸው፡፡ ከጥያቄዎቹ ውስጥ በግልጽ መልስ ያገኙ የምላቸው፡ ከየትኛው ህዝብ ነህ? ሥራህ ምንድነው? የሚለውና በማን ምክንያት ይህ ደረሰብን የሚሉት ናቸው፡፡
6. ዮናስ ማንነቱን ሲነግራቸው ሰዎቹ ድንጋጤ እንደተሰማቸውና ከዚህ ከደረሰባቸው ነገር መዳን የሚችሉት በምን መንገድ እንደሆነ ለዮናስ ለራሱ ጥያቄ ሲያቀርቡለት ነው የሚታየው፡፡ በመፍትሔነት የነገራቸው ነገር፤ እርሱን አንስተው ወደ ባህር ቢጥሉት ማዕበሉ ጸጥ እንደሚል ነው፡፡ በቁ13 ላይ ዮናስን ለማዳን ወደ የብስ ለመድረስ ባላቸው ሃይል ሁሉ እየቀዘፉ መሞከራቸው ነገር ግን አለመቻላቸው ነው፡፡
7. የመርከቢቱ ተሳፋሪዎች ማዕበሉ ከአቅማቸው በላይ ስለሆነባቸው ዮናስን ወደ ባህሩ መጣል ግድ ነበረና ወደ ባህር እንደወረወሩት እናነባለን፤ በዚህን ጊዜ ባህሩ መናወጡን ስላቆመ ሰዎቹ እግዚአብሄርን እጅግ እንደፈሩና መስዋዕትን እንዳቀረቡለትና ስለትንም ሲሳሉ እንመለከታለን፡፡
8. በሁኔታዎቹ ውስጥ ሲጎሳቆሉና መፍትሔ ለማግኘት ሲጥሩ የምናያቸው የመርከቢቱ ተሳፋሪ የነበሩት ሰዎች ናቸው፡፡ ለዚህ መከራና ጥፋት ሁሉ ግን ምክንያትና መነሻ የሆነው ዮናስ እንደሆነ ራሱ ሲናገር እንመለከታለን፡፡

# ጥናት ሁለት ዮናስ 1፡17-2፡10

1. ዮናስ ወደ ባህር ሲወረወር እግዚአብሄር እርሱን የሚውጥ አሳ አዘጋጀ። እኔ ከእግዚአብሄር ባህርይ እንደተረዳሁት፤ የመረጣቸውን ባሮቹን ሲደክሙና ሲያጠፉ እነርሱን እየጣለ ሌላ የተሸለ ሰው በማምጣት ስራውን መስራት ሳይሆን ሃሳቡ፤ የደከሙትንና እንቢተኞቹን በመቅረጽና በማስተካከል እርሱ የሚፈልግበት ደረጃ ማድረስ እንጂ እያነሱ መጣል የእርሱ ባህርይ እንዳልሆነ ነው የማምነው። ለእኔም የዚሁ ዓይነት ምህረት እንደሚያሳየኝ እንጂ ደከመ ወይም እንቢተኛ ሆነ ብሎ አይተወኝም ማለት ነው።
2. በማቴ 16፡4 ላይ የዮናስ በዓሳ ሆድ ውስጥ ማደር ተዓምራት እንደነበረ፣ ኢየሱስም ሶስት ቀንና ሶስት ሌሊት በምድር ከርስ አድሮ መውጣቱ ተአምር መሆኑን፣ በማቴ 12፡40 ደግሞ ኢየሱስም እንደ ዮናሰ ሶስት ቀናትና ሶስት ሌሊት እንደሚቆይ ማስታወቅ፣ ሉቃ 11፡30 ላይ የዮናስ ለሶስት ቀንና ለሶስት ሌሊት በአሳ ሆድ ውስጥ አድሮ መውጣት ለነነዌ ሰዎች መልዕክቱን ለመቀበል በምልክትነት እንዳገለገለ ሁሉ፣ የኢየሱስም በምድር ከርስ ውስጥ አድሮ መነሳቱ ለትውልዱ ሁሉ የተልዕኮውን እውነተኛነት ያረጋግጣል ማለት ነው።
3. በደህናው ጊዜ ሲያደርግ ያላየነውና በዓሳው ሆድ ውስጥ ሲያደርግ የምናየው ወደ አምላኩ ወደ እግዚአብሄር መጸለይ ነው። የተጣራባቸው ሁለት ምክንያቶች የመጀመሪያው ‹‹ተጨንቄ ሳለሁ›› የሚለው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ‹‹ርዳታን ፈልጌ›› የሚለው ሃሳብ ነው።
4. ዮናስን ወደ ባህሩ የጣሉት ራሳቸው የመርከቢቱ ተሳፋሪዎች ሲሆኑ፤ ዮናስ ግን በዚህ ቁጥር ላይ እየተናገረ ያለው ነገር እርሱ የራሱን እንቢተኛነትና እግዚአብሄር ደግሞ ለዚህ ለእንቢተኛነቱ እየተከታተለ በተፈጥሮ ሁሉና በሰዎችም ሁሉ በመጠቀም የሚሆነውን ሁሉ የሚያቀናጀው እግዚአብሄር አንደሆነ ስለሚያውቅ ነው የዚህ ዓይነት አነጋገር እየተናገረ ያለው።
5. ቁ4 ላይ ያለውን ሃሳብ ስናነብ ‹‹እንደገና ወደ ቅዱስ መቅደስህ እመለከታለሁ አልሁ።›› የሚለው አነጋገሩ በልቡ የመመለስ ውሳኔን እንዳደረገ ያሳየናል። ውሃ እስከ አንገቱ እንዳጠለቀው፣ ጥልቁም እንደከበበው፣ የባህር ዓረም በራሱ ላይ እንደተጠመጠመበት፣ ወደ ተራሮች መሰረት እንደሰመጠና፣ የምድር በር ለዘለዓለም እንደተዘጋበት እንደተሰማው ይናገራል።
6. ዮናስን ወደ ባህር ውስጥ ያወረደውና ከባህር ውስጥ ሊወጣ ሁለቱንም ማድረግ የቻለው እግዚአብሄር ራሱ እንደሆነ ሁሉ፤ በ1ኛ ሳሙ 2፡6-7 ውስጥም በሃና አንደበት የተነገረው እግዚአብሄር የመግደልና የማዳን፣ ወደ ሲዖል የማውረድና ከሲዖልም የማውጣት፣ ድሃም ሆነ ባለጠጋ የማድረግ፣ ማዋረድም ሆነ ከፍ ከፍ ማድረግ የሚችል አምላክ መሆኑን የዮናስ የህይወት ልምምድና የሃና አነጋገር በመስማማት ያስተምሩናል።
7. ዮናስ የሚያወዳድራቸው ሰዎች የመጀመሪያዎቹ፤ ከንቱ በሆኑ ጣዖቶች ላይ የሚንጠላጠሉና፣ ሌሎቹ ደግሞ እንደ ዮናስ በምስጋና መዝሙር ለእግዚአብሄር መስዋዕት የሚሰው ናቸው። በጣዖት የመታመን ውጤቱ ከእግዚአብሄር ሊቀበሉ የሚችሉትን በረከትና ጸጋ ያጣሉ፣ በእግዚአብሄር የመታመን ውጤቱ ደግሞ ቁ9 እንደሚነግረን ደህንነት እንደሆነ ነው። ዮናስን ታዞ የዋጠው አሳ፤ በዚህ ክፍል ደግሞ ለእግዚአብሄር ታዞ ሲተፋው እናነባለን።
8. ዮናስ ነፍሱ በዛለችበት የወሰዳቸው ሁለት አስፈላጊ እርምጃዎች፤ እግዚአብሄር አምላኩን ማሰብና፣ ሌላው ደግሞ ወደ አምላኩ ጸሎቱን ማሰማት ነበረ።

# ጥናት ሶስት ዮናስ 3፡1-10 (ለመሪው የተዘጋጀ)

1. ዮናስ በንስሃ ልቡን ወደ አምላኩ ሲመልስ እግዚአብሄር ደግሞ ሌላ ሁለተኛ እድል ሲሰጠውና ተልዕኮውን ሲያድስለት ነው የምናየው።
2. ዮናስ ለነነዌ ህዝብ እንዲናገር የታዘዘው ‹‹የምነግርህን መልዕክት ስበክላት›› ስላለው እግዚአብሄር የሚናገረውን ብቻ እንዲነግራቸው ነው። የመጀመሪያው መልዕክት ለዮናስ ባይስማማውም እግዚአብሄር ግን ሁለተኛም ሲልከው መልዕክቱን አልቀየረውም፤ ምክንያቱም እግዚአብሄር እርሱ ራሱ እንጂ መልዕክቱን ባሪያዎቹ ሊቆጣጠሩት አይፈቅድምና ነው።
3. በምዕራፍ አንድ ውስጥ ዮናስ ተልዕኮውን እንቢ ብሎ ከእግዚአብሄር ፊት ሲኮበልል ስናይ በምዕራፍ ሶስት ውስጥ ደግሞ ዮናስ የእግዚአብሄርን ተልዕኮ ሲታዘዝ ይታያል። በመጀመሪያው ምዕራፍ ወደ ነነዌ ሲላክ ወደ ተርሴስ እንደሄደ ስናይ፤ በሶስተኛው ምዕራፍ ደግሞ ወደ ነነዌ ሲላክ ወደ ነነዌ እንደሄደ እናነባለን። በዚያን ጊዜ ነነዌ ታላቅ ከተማ እንደነበረችና፣ ነነዌን ከዳር እስከዳር ሄዶ ለመጨረስ ሶስት ቀን ያህል እንደሚያስፈልግ ይነገርናል።
4. ለነነዌ ሰዎች የዮናስ ስብከት ‹‹ነነዌ በአርባ ቀን ውስጥ ትገለበጣለች›› የሚል ነበረ። እግዚአብሄር ለነነዌ ሰዎች ንስሃ እንዲገቡ የሰጣቸው አርባ ቀናት እንደነበረ እንመለከታለን።
5. የነነዌ ሰዎች በእግዚአብሄር እንዳመኑ፣ ጾምን እንዳወጁና፣ ከትልቁም ጀምሮ እስከ ትንሹ ድረስ ማቅ እንደለበሱ እናነባለን። ይህ የንስሃ ስብከት አምስት ቃላቶችን ብቻ ያዘለ በመሆኑ፤ ምናልባትም ደጋግሞ ካላለው በስተቀረ ከአስር ሰከንድ እንደማበልጥ እናውቃለን። ሰዎችን ወደ ንስሃ ለማምጣት የሚያስፈልገው የእኛን መታዘዝና የሰዎቹ ልብ መዘጋጀት እንደሆነ መማር እንችላለን።
6. የነነዌ ንጉስ የዮናስን ዓዋጅ ዜና በሰማ ጊዜ ከዙፋኑ ወረደ፣ ልብሱን አወለቀ፣ ማቅ ለብሶ በአመድ ላይ ተቀመጠ፣ አዋጅ አስነገረ። ዐዋጁ የሚመለከተው ሰውን ሁሉ፣ እንስሳን፣ የከብት መንጋና የበግ መንጋን ሁሉ ነበረ። ትዕዛዙም ምንም ነገር እንዳይቀምሱ፣ ውሃ እንዳይጠጡ፣ ማቅ እንዲለብሱ፣ ወደ እግዚአብሄር አጥብቀው እንዲጮሁ፣ ሰዎች ሁሉ ክፉ መንገዳቸውንና የግፍ ሥራቸውን እንዲተው የሚል ነው። ሰዎቹም ሆኑ ንጉሱ የእግዚአብሄርን አዋጅ በደንብ ትኩረት እንደሰጡት ነው የማየው።
7. የተናገሩትን ሰምቶ አይደለም፤ ነገር ግን ያሰበውን ይፋት ከማድረግ የተመለሰው ‹‹ምን እንዳደረጉና ከክፉ መንገዳቸውም እንዴት እንደተመለሱ ባየ ጊዜ›› ብሎ ነው የሚናገረው።
8. በዚህ ክፍል ተገልጦ የምናየው የእግዚአብሄር ባህርይ ርህራሄው ነው። እግዚአብሄር የአይሁድ አምላክ ብቻ ሳይሆን አህዛብንም የሚወድ ከልባቸው ወደ እርሱ የሚመለሱትን ሁሉ የሚቀበል አምላክ እንደሆነ እንማራለን።

# ጥናት አራት ዮናስ 4:1-11

1. የነነዌ ሰዎች ንስሃ መግባትና፣ እግዚአብሄር ደግሞ ይቅር ማለቱ ዮናስን በጭራሽ ደስ አላሰኘውም፤ እንዲያውም ቁ1ድን ስናነብ ዮናስ ተቆጣ ይላል። አስቀድሞም ዮናስ ለእነዚህ ሰዎች የንስሃን እድል እንዲሰጣቸው የንስሃን መልዕክት ይዞ እንዲሄድ ሲጠየቅ በእንቢተኛነት መኮብለሉ ከዚሁ የተነሳ ሲሆን፤ ለነዚህ ሰዎች ግድ ሆኖበት እንጂ ሁለተኛውንም ተልዕኮ የተቀበለውም በደስታ አልነበረም።
2. ዮናስ በተቆጣ ጊዜ ማድረግ የፈለገው ወደ እግዚአብሄር መጸለይና ደስተኛ አለመሆኑን መግለጽ ነው። እኔ ይህ ነብይ ከአገሩ ከመውጣቱ በፊት ከእግዚአብሄር ጋራ ያደረገው ውይይት በቁ2 ላይ እንደሚናገረው እግዚአብሄር ምንም ያህል ክፋትን ቢጠላም ሰዎች ተመልሰው በይቅርታ ከቀረቡት የሚራራና ይቅር የሚል አምላክ መሆኑ ስለገባው እነዚህ የእስራኤል ጠላቶችም ይቅር የመባል ዕድል ሊገጥማቸው መቻሉን ያነጋገረው ይመስለኛል።
3. ወደ ተርሴስ ለመኮብለሉ ምክንያት እንደሆነ በቁ2 ላይ የሚናገረው ሃሳብ ለነነዌ ህዝብ የንስሃ መልዕክት በማቅረብ ለእግዚአብሄር ይቅርታና ምህረት ላመቻቸቸው አልፈልግም በሚል ነው። ዮናስ ግልጽ አድርጎ በቁ2 ላይ የሚናገራቸው የእግዚአብሄር ባህርያት፡ ቸርነቱ፣ ርህራሄው፣ ምህረቱ፣ ከቁጣ የራቀ መሆኑና ጥፋትን ከማምጣት የሚመለስ አምላክ እንደሆነ ይዘረዝራል።
4. እነዚህ የነነዌ ሰዎች አለምን ሁሉ በማንቀጥቀጥ የገዙ፣ ምህረት ማድረግ ያለመዱ ጨካኞች ስለሆኑ፤ በተለይም ደግሞ በእስራኤልን ህዝብ ያጎሳቆሉ ስለሆኑ የአበር ወዳድነት ስሜት ብቻ ሳይሆን የክፋታቸውንም ጥላቻ ሲያንጸባርቅ ነው። ነብዩ ዮናስ በስብከቱ ብዙ ሰው መዳኑ ከሚያስደስተው ይልቅ በቁ3 ላይ እንዲያውም፤ በሆነው ነገር ደስ አለመሰኘቱን ጥልቀቱን የሚያሳየንን ነገር ለአምላኩ ሲናገር ‹‹ከምኖር መሞት ይሻለኛል›› በማለት ከባድ የሆነ አነጋገር ሲናገር ይታያል።
5. እግዚአብሄር ዮናስ ተቆጥቶ ሲናገር ያደረገው ነገር ጥያቄ ማቅረብ ነበረ።‹‹በውኑ ልትቆጣ ይገባሃልን?›› ። ዮናስ ያደረገው ለጥያቄው መለስ ሳይሰጥ ከከተማይቱ ወጥቶ ለራሱ ዳስ ሰርቶ በመቀመጥ፣ በነነዌ ከተማ ላይ የሚሆነውን ነገር ለመመልከት ከዳሱ ጥላ ስር እንደተቀመጠ ይታያል። ኢኔ እንደሚመስለኝ አነዚህን ሰዎች ሲያውቃቸው እንደዚሁ በቀላሉ የማይመለሱና መመለሳቸው ራሱም ሊያስመስሉ ሊሆን ይችላል በሚል ተስፋ ያለ ነው የሚመስለኝ።
6. ዮናስ ከነበረው ቃጠሎ ልታሳርፈው የምትችለውን ቅል ስላበቀለለት የተሰማው ደስታ እንደነበረ እናነባለን።
7. የመጀመሪያ ላይ ዮናስን ሞት ያስመኘው የሰዎች ንስሃ ገብቶ ይቅርታ መቀበላቸው ሲሆን፤ ሁለተኛው ደግሞ ዮናስን ከነበረበት የተበላሸ አመለካከት ውስጥ ለማውጣት እግዚአብሄር የተለያዩ ሁኔታዎችን በማቀነባበር እየወሰደ ባለው እርምጃ የተነሳ ዮናስ የተሰማው ስሜት ነው። እነዚህን የተለያዩ ፍጥረቶቹን በፈለገው መንገድ እንዲወጡና እንዲገቡ ሲያዝ ስናይ፤ ሊያስተምረን የሚችለው ነገር እግዚአብሄር ፍጥረትን ሁሉ የሚገዛና የሚቆጣጠር አምላክ እንደሆነ ነው።
8. ዮናስ እንዲገባውና እንዲረዳለት የፈለገውን ነገር በአንድ ዓረፍተ ነገር ማስቀመጥ ቢያስፈልግ፤ ‹‹ለአይሁድ ብቻ ሳይሆን ለአህዛብም ርህሩህ ነኝ›› ማለት ይቻላል።
9. እግዚአብሄር ሥራው መሰራቱን ብቻ የሚፈልግ አምላክ ሳይሆን፤ በምን አይነት መንፈስና ምን ዓይነት አስተሳሰብ ይዞ እንደሚሰራ ግድ ስለሚለው፤ ዮናስን የተከታተለበት ምክንያት ምክንያት አስተሳሰቡን ለመቀየር ነው።